Newsletter

# ETHIOPIAN COMMUNITY ASSOCIATION OF CHARLOTTE & SURROUNDING AREAS
# የሻርለት እና አካባቢው የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ ማኅበር

November 2022 / Vol 2

## Upcoming Events

**Sunday, November 6**
**Open House at Providence Day School**
5800 Sardis Rd, Charlotte, NC 28270
2:00PM

**Saturday, November 19**
**Health and Life Insurance Enrollment**
5535 Albemarle Rd, Charlotte, NC 28212
2:00 PM

**See how you can take advantage of program offered by:**

CTAC

**Career Technology Apprenticeship Cohort**

Graduates have been hired by...

usbank, TRUIST, LOWE'S, WELLS FARGO, ally, BANK OF AMERICA

... and more

## Community Highlight- Feven Fanta

**ECAC received the following testimonial about how information a member of our community received from ECAC in 2021 about IT training opportunity by a local non-profit organization, CTAC, helped to change her life!**

My name is Feven Fenta and I have been in Charlotte for 2years.

I heard about the Ethiopian Community Association of Charlotte on Facebook.

I am here to give my testimony about **CTAC (Career Technology Apprenticeship Cohort) https://stiegleredtech.org/ctac** program that was shared on your page about the opportunity to get paid to learn programming and to gain employment after training.

**በኮሚዩኒቲው አማካይነት ባገኘችው መረጃ አማካይነት የሥራ ሕይወቷን ለመለወጥ ከቻለቸው የአካባቢያችን ነዋሪ ከእህታችን ከወ/ሮ ፌቨን ፈንታ ጋር የተደረገ አጭር ቆይታ**

**ጥ፡ እህታችን ፌቨን ስምሽንና ራስሽን ብታስተዋዉቂን?**

መ:ለመጀመር ያህል ሥሜ ፌቨን ፈንታ ይባላል። ባለትዳር እና የአንድ ወንድ ልጅ እናት ነኝ።

**ጥ፡ በሻርለት ከተማ ምን ያህል ኖርሽ?**

መ፡ ወደሻርለት መጥቼ መኖር ከጀመርኩኝ ሁለት ዓመት ሆኖኛል።

**ጥ፡ ስለሻርለት የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ እንዴት ሰማሽ እንዴትስ አገኘሽዉ? የምታዉቂዉን ያህል ብታጫዉቺን?**

መ፡ የሻርለት የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲን ያወቅሁት በጓደኞቼ ፌስቡክ ላይ ሼር ተደርጎ በማየት ነዉ። ከዚያ በኋላ ስለኮሚዩኒቲዉ ከማዉቃቸዉ ጥቂት ሰዎች በጣም ደስ የሚልና በጎ ነገሮችን መስማት ችያለሁ እንዲሁም መስማት ብቻ ሳይሆን...

...continued on page 2

Newsletter
ETHIOPIAN COMMUNITY ASSOCIATION OF CHARLOTTE & SURROUNDING AREAS
የሻርለት እና አካባቢው የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ ማኅበር
November 2022 / Vol 2

## Community Highlight- Feven Fanta (Continued)

The program is a 24-week intensive training course. The first step is to complete an untimed initial assessment and if selected, to go through the interview process.

As indicated on CTAC website “A motivated adult who may not have a traditional route to explore technology opportunities and has a strong interest in careers within the technology industry. Candidates also display a high aptitude for learning and are ready, willing, and able to do what it takes to be successful in a game-changing career.”

The program is completely different from other bootcamps. First, You will get paid to learn programming. Second, it also guaranteed placement after graduation.

Graduation and placement is guaranteed based on the passing of exams and submission of projects on time.

I would like to thank the ECAC for sharing the information and to my husband Dani, my Mom Almi, Lidu, Gelilu and Ellu for all the support. Finally, I want to express my gratitude to the CTAC program for giving me the chance and a way to land my first job in technology.

...ኮሚዩኒቲዉ ከሚሰራዉ መልካም ሥራ በረከት ተካፋይ ለመሆን ችያለሁ፤ ስለዚህም እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። እንዲሁም የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲን እጅግ ከቤ አመሰግናለሁ፤ ደግሞም በርቱ በዚሁ ቀጥሉ እላለሁ።

**ጥ፡ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲን ዛሬ ልታገኚዉና የክብር እንግዳ ሆነሽ በበኮሚዩኒቲዉ መጽሔት ላይ ምስክርነት ለመስጠት የመጣሽበት ጉዳይ ምን ይመስላል?**

መ፡ እኔ ዛሬ በኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ በተከፈተልኝ መልካም እድል በመጠቀም **የ CTAC (Career Technology Apprenticeship Cohort)** ተጠቃሚ ሆኛለሁ። ባገኘሁት መረጃ መሰረት እድሉን ተጠቅሜ የ24 ሳምንት ስልጠናዉን በመዉሰድ ዛሬ የቴክኖሎጂ ባለሙያ ሆኜ ጥሩ ሥራ እየሰራሁ እገኛለሁ። ይህንንም መልካም እድል እንዳገኝ ኢንፎርሜሽን ፍልጎ ለኮሚዩኒቲዉ እንዲደርስ ጠንክሮ እየሠራ ያለዉን የኢትዮጵያ ኮሞዩኒቲን ለማመስገንና ሥራቸዉንም ለማበረታታት ሲሆን እንዲሁም ደግሞ ለሌሎችም ይህ እድል የመጪው ዓመት የምዝገባ ጊዜ ሳያልፍ እንዲደርስ ለማገዝ ያህል ነዉ።

**ጥ፡ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ የጠቀመሽ መረጃ በመስጠት ሲሆን ከዚያ በኋላ የሄድሽበት መንገድ ምን ይመስላል?**

መ፡ ከላይ እንደጠቀስኩት መረጃው እንደደረሰኝ ወዲያዉኑ ተመዘገብኩኝና የመመዝገቢያ ፈተናዉን (initial assessment) ወስጄ ከተወሰኑ ቀናት በኋላ ለቃለ መጠይቅ (ኢንተርቪው) ተጠራሁ፤ ይህንንም ማጣሪያ ካለፍኩ በኋላ ትምህርቱን እስክጨርስ በሰዓት እየተከፈለኝ በጣም ጥሩ እዉቀትን የሚገነባ ትምህርት እየተማርኩኝ የ24 ሳምንቱን (ሰድስት ወር ማለት ነው) የስልጠና ግዜ አጠናቅቄ እግዚአብሔርም እረድቶኝ የሥራ እድል በፕሮግራሙ አማካይነት አግኝቼ ለመጀመር ችያለሁ።

**ጥ፡ ትምህርቱን መጀመር ለሚፈልጉ ማስተላለፍ የምትፈልጊዉ መልክት አለ? ምን ዓይነት ዝግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል?**

መ፡ ትምህርቱን መጀመር ለሚፈልጉ ማስተላለፍ የምፈልገዉ መልክት የመጀመሪያዉን የመመዝገቢያ ፈተናዉን (initial assessment) ፈተና ሳትዘናጉ በደንብ ሥሩት፣ ከዚያ በኋላ ደግሜ ለኢንተርቪዉ ስትጠሩ የተወሰኑ ነገሮችን በተለይ Java፣ HTML እና የመሳሰሉትን ለማንበብ መሞከርና መዘጋጀት በጣም ይጠቅማል እላለሁ።

Newsletter

# ETHIOPIAN COMMUNITY ASSOCIATION OF CHARLOTTE & SURROUNDING AREAS
# የሻርለት እና አካባቢው የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ ማኅበር

November 2022 / Vol 2

CTAC

## SPRING 2023 TIMELINE

**NOW → JAN. 9. 2023**
**APPLY FOR THE NEXT CTAC COHORT.**
**(HTTPS://SURVEY.STIEGLEREDTECH.ORG/ZS/NVD7OI)**
**MAKE SURE TO GIVE YOURSELF ADEQUATE TIME!**

**DEC. 26. 2022 → FEB. 6. 2023**
THE INTERVIEW PROCESS BEGINS.
NOTE: IF YOU APPLY AFTER 12/26, YOUR APPLICATION WILL STILL BE REVIEWED.

**FEB. 6. 2023**
APPLICANTS RECEIVE OFFER LETTER.
NOTE: IF YOU ARE NOT ACCEPTED, YOU WILL ALSO BE NOTIFIED

**MAR. 6. 2023**
DAY 1 OF THE 24-WEEK COHORT BEGINS!

**ጥ፡ ትምህርቱን ወይም ስልጠናዉን ለመጨረስ ምን ያህል ግዜ ፈጀብሽ?**

መ፡ ፕሮግራሙ በቀናት የተቀመጠ ስለሆነ መዘግየት አይቻልም፤ ትምህርቱ ከተጀመረ በኋላ ከሁሉም ተማሪዎች ጋር በ24 ሳምንት ነዉ የጨረስኩት።

**ጥ፡ ትምህርቱ ክፍያ አለዉ ወይስ በነጻ ነዉ? ክፍያስ ካለዉ ምን ያህል መገመት ይቻላል?**

መ፡ ትምህርቱ ምንም ዓይነት ክፍያ የለዉም እንዲያዉም ለተማሪዎች ትምህርታቸዉን እስኪጨርሱ ድረስ በሰአት ከ $14.00-$17.00 ዶላር ትምህርት ቤቱ ይከፍላል።

**ጥ፡ አንቺ የወሰድሽዉን ስልጠና በሌሎች መሰል ትምህርት ቤቶችና ተቋማት ከሚሰጡ ስልጠናዎች ለየት የሚያደርገዉ ምንድ ነዉ?**

መ፡ ይህንን ትምህርት ቤት ለየት የሚያደርገዉ በትዳር ዉስጥ ያሉ፣ ልጆች ያላቸዉ እንዲሁም የመማር ፍላጎትና አቅም እያላቸዉ በኑሮ የተለያዩ ሀላፊነቶች ጫና መማር ላልቻሉ ሰዎች እጅግ ትልቅ እድል ነዉ ምክንያቱም ትምህርት ቤቱ የሚከፍለዉ ገንዘብ ለተወሰነ ጊዜ በፕሮግራም በመኖር ቤትና ኑሮን ሳይጎዱ ተጨማሪ የትምህርት ቤት እዳ ሳይይዙ መጨረስና መማር ማስቻሉ፣ እንዲሁም ከተመረቁ በኋላ ደግሞ በቀጥታ በራሱ ሥራ በተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ማስቀጠሩ ልዩ ያደርገዋል። እዚህ ማሰልጠኛ የተማረ ሰዉ ከእግዚአብሔር ጋራ ያለምንም ኮንትራት 100% ሥራ የማግኘት እድሉ የተረጋገጠ መሆኑ፣ ሥራ ለመቀጠር የኢንተርቪዉም ሆነ ሌላ ክፍያ ሳያስቡ ምናልባትም ኢንተርቪዉ እንኳን ሳይደረጉ ሥራ የመቀጠሩና የመጀመሩ እድል በጣም ልዩ ያደርገዋል።

**ጥ፡ ከዚህ በፊት ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርስቲ ገብተዉ ያልተማሩና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ብቻ ያጠናቀቁ ሊማሩት ይችላሉ?**

መ፡ አዎ በጣም ይችላሉ። የሚያስፈልገዉ ትምህርቱ የሚጠይቀዉን የጊዜ አጠቃቀም ዲሲፒሊን ማክበርና ማጥናት ብቻ ይመስለኛል።

**ጥ፡ በመጨረሻ ማስተላለፍ የምትፈልጊዉ ተጨማሪ መልዕክት ካለ እድሉን እሰጥሻለሁ፦**

**መ፡** በመጀመሪያ በድጋሚ በሁሉ የረዳኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ። እንዲሁም ይህንን መረጃ በትጋት በመፈለግ ለማህበረሰባችን ጠቃሚን ሥራ እየሠራ ያለዉን የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲን ከልቤ አመሰግናለሁ። በዚህ የትምህርት ቆይታ ዉስጥ ደግሞ ከጎኔ የነበረዉን ባለቤቴን ዳኒን፣ እናቴን አልሚን፣ ሊዱን፣ ገሊሉን እና ኤሉን ስላደረጋችሁልኝ እገዛና ትብብር ከጎኔ ስለቆማችሁ እግዚአብሔር ያክብርልኝ፤ ከልቤ አመሰግናለሁ ለማለት እወዳለሁ። በመጨረሻም CTAC ን ስለሰጠኝ የትምህርት እድልና የመጀመሪያዉን የቴክኖሎጂ ሙያ ሥራዬን ለማግኘትና ለመጀመር መንገድ ስለሆነኝ ማመስገን እፈልጋለሁ። እድሉን በማግኘት ለመማር ለሚዘጋጁና ለሚጀምሩ መልካም እድል፣ በርቱ እላለሁ፣ አመሰግናለሁ።